# 1. መግቢያ

በማንኛውም የታክስ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ የግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ተቀዳሚ ተግባራት

* ግብር ከፋዩን ለይቶ ማወቅ
* ግብርና ታክስ መወሰን
* የተወሰነውን ግብርና ታክስ መሰብሰብ
* ግብር ከፋዩን ማስተማርና መደገፍ
* ሕግ ማስከበር የመሳሰሉት እና ሌሎችም ናቸው፡፡

ከዚህ አንፃር ቀዳሚው ተግባር እውን ይሆን ዘንድ የግብር ከፋዩን ማንነት ፡-

* በስም
* በአድራሻ
* በተሠማራበት የሥራ ዘርፍ ... ወዘተ ለይቶ መመዝገብ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ለዚህ ተግባር እንዲያመችም በተለያዩ ሃገሮች የተለየዩ የግብር ከፋይ መለያ ሥርአት ተግባራዊ ቢሆንም /በአብዛኛው ሃገሮች እየተሰራበት ያለውን/ የግብር ከፋዩ መለያ ቁጥር /Tax payers Identification Number-TIN/ አሠራር በሃገራችን መዘርጋት የግድ ይሆናል፡፡ ለግብር ከፋይ ልዩ የመለያ ቁጥር /TIN/ የመስጠት አሠራር የዘመናዊ ግብር /ታክስ አስተዳደርን ተግባራዊ ያደረጉ ሃገራት ግብር ከፋዮቻቸውን በቀላሉ ለይቶ ለማወቅና ኢኮኖሚያዊያዊ እንቅስቃሴያቸውን ለመከታተል የዘረጉት የአሰራር መርህ ነው፡፡

አሠራር ሥርአቱ የመረጃ ቴክኖሎጂን አጠቃቀም መሠረት ያደረገ በመሆኑ ለግብር አሰባሰብና አወሳሰን የሚረዱ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ለማጠናቀርና ለማሠራጨት እንዲሁም ለግብር ከፋዩ ህብረተሰብ የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ዘመናዊ አሰራር ነው ፡፡

## *2. <u>የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ ምንነት</u>*

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር / Tax payers Identification Number-TIN / በግብር ከፋይነት የተመዘገበ ግለሰብ ወይም ድርጅት በዘመናዊ የኮምፒዩተር አሠራር ሥርዓት በውስጠ ታዋቂ ስሙን የሚተከ ቁጥር በመስጠት በቀላሉ ማንነቱን የሚለይበት ዘዴ ነው፡፡

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት ብዙ ቅርንጫፎችም ቢኖሩት በአንድ ስም ብቻ የሚመዘገብ፣አንድ ጊዜ እና አንድ ብቻ መለያ ቁጥር የሚሰጥ ነው፡፡ ማለትም አንድ ግብር ከፋይ ከአንድ በላይ መለያ ቁጥር እንዲይዝ የማይፈቅድ የአሠራር ሥርዓት ነው፡፡

## *3. <u>የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ አሰጣጥ እንዴትና ለምን ተጀመረ ?</u>*

በቀደምት የግብር ከፋይ ምዝገባ አሠራር ሥርዓት አንድ ግብር ከፋይ የንግድ ሥራውን በሚያካሂድበት ቦታ /ወረዳ አውራጃ ክ/ሃገር/ በሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ተመዝግቦ ፤ የተለያየ ኮድ እና ቁጥር በመስጠት በባህር መዝገብ ሰፍሮ ማህደር ወይም ፋይል ይከፈትለት ነበር ፡፡ ይህ አይነቱ አሠራር መ/ቤቶች መረጃ የሚለዋወጡበትን ሁኔታ ያመቻቸ ባለመሆኑ የግብር ከፋይ ኮድና ቁጥር ጥቅም ላይ የሚውለው ግብር ከፋዩ በተመዘገበበት መ/ቤት ለውስጥ አገልግሎት ብቻ ነበር፡፡ ለአብነትም ለፖስፖርትና ቪዛ፣ ለጡረታ መክፈያ ወዘተ፡፡ ስለግብር ከፋይ በመ/ቤቶች መካከ1ል የሚደረገው የመረጃ ልውውጥ በማኑዋል ስለነበር ጊዜ ወሳጅ እና ጥራት የጐደለው ነበር፡፡

ይህን ጉድለት ለማስወገድና የግብር/ታክስ አስተዳደርን ዘመናዊና ቀልጣፋ ለማድረግ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አሰጣጥ የራሱ ዘመናዊ አሠራር /Soft ware/ ያለው፤ በመረጃ መረብ /LAN & WAN/ አማካይነት በተለያዩ ቦታ የሚገኙ መ/ቤቶች መካከል ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር የሚያስችል የመለያ ቁጥር /TIN/ አሰጣጥ ሥርዓት በመዘርጋት ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

## 4. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር/TIN/ ዓላማ

የግብ ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ ዋና ዓላማ የታክስ ባለሥልጣኑን

- Φ ግብር/ታክስ መክፈል የሚገባውን ግለሰብ ወይም ድርጅት የተሠማራበትን የሥራ ዘርፍ፤ አድራሻ፣ የቀን ወይም የዓመት ጠቅላላ ገቢና የሚከፈለው የግብርና ታክስ አይት ለይቶ ለማወቅ፣
- Φ ግብር/ታክስ በወቅቱ አስታውቀው የሚከፍሉና የማይከፍሉ ግብር ከፋዮችን ለመቆጣጠር የሚያስችል አሠራርን ለመዘርጋት፣
- Φ ከሦስተኛ ወገን የሚገኝ የግብር ከፋዩን መረጃ በተጠናከረ ሁኔታ በአግባቡ ሰብስቦ ለመያዝ እና ግብር ከፋዩ ከሚያቀርበው መረጃ ጋር በቀላሉ ለማመሳከር የሚያስችል የአሠራ ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡
- Φ ግብር ከፋዩ ህብረተሰብ በትክክለኛ መረጃ የተመሰረተ ግብርና ቀልጣፋ አገልግሎት በወቅቱ እንዲያገኝ ለማድረግ ነው፡፡

## 5. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ አስፈላጊነትና ጥቅም

- Φ የግብር ከፋዩ መለያ ቁጥር /TIN/ አሠራር ግብር ሰብሳቢ መ/ቤቱን ለግብር አሰባሰብና አወሳሰን የሚረዱ መረጃዎችን በጥራት ለማሰባሰብ ለማጠናቀርና ለማሠራጨት ያስችለዋል፡፡፡

- Φ ግብር ከፋዩ ህብረተሰብ ፍትሃዊ በሆነና የራሱን ድርሻ በለየ መልኩ ግብር የመክፈል ግዴታውን በፈቃደኝነት እንዲወጣ ያስችላል፡፡

- Φ ዘመናዊ የኮምፒዩተር መረጃ ቴክኖሎጂን በመጠቀም በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቱና በሦስተኛ ወገን መካከል የመረጃ ልውውጥ ለመዘርጋት እና የታክስ አሰባሰብ ሂደቱን ቀልጣፋ እንዲሆን አስችላል፡፡

- Φ በማንኛውም ጊዜ በንግድ ሥራ ላይ የሚገኙ ግብር ከፋይንና ሥራውን የዘጋ /Active and dead files/ ማህደር በመለየት የጠራ የግብር ከፋይ መረጃ እንዲኖር ያስችላል፡፡

- በግብር አወሳሰን ሂደት ግብር ከፋይ የሚገልጸው የግዢ ወይም የሽያጭ ገቢ መጠንና ሌሌች መረጃዎችም በመለያ ቁጠር አማካይነት ከሌሎች መ/ቤቶች ከሚገኝ መረጃ ጋር ለማገናዘብ ያስችላል፡፡

- የግብር ሰብሳቢ መ/ቤቶች ስለግብር ከፋዩ የሚፈለጉትን መረጃ በቀላሉ ለማግኘት ይረዳል፡፡

- ከማናቸውም ምንጭ የሚገኘውን የአንድ ግብር ከፋይ መረጃ በመለያ ቁጥሩ አጠናቅሮ በመያዝ የታክስ ተመላሽ ጥያቄን በወቅቱ ለማስተናገድ፣ በኮምፒዩተር የታገዘ የ3ኛ ወገን የታክስ አሰባሰብ ሥርዓት ለመዘርጋት

- በግብር ባለሥልጣኑ፤ በመንግስት መ/ቤቶች፣ በባንኮች፣ በንግድ ድርጅቶች እና በሌሎች ተቋማትም ጭምር ግብር ከፋዩን የሚለዩበት አንድ ወጥ መለያ /standard identification/ ሥርአት እንዲኖር ያስችላል፡፡

- በአጠቃላይ በሃገር አቀፍ ደረጃ የግብር ከፋዩ መለያ ቁጥር አሰጣጥ ሥርዓትን በመዘርጋት በህብረተሰብ ውስጥ የግብርና ታክስ ህግና ድንጋጌዎችን አንድ ወጥ በሆነ መንገድ በብቃትና በእኩልነት ተግበራዊ ለማድረግ የጠቅማል፡፡
- ሀገራችን እያደገችና እየበለጸገች በሄደች መጠን ሌሎች የበለጸጉ ሀገራት እንደሚገለገሉበት የማህበራዊ ደህንነት መለያ ቁጥር /Social Security Number/ ኢትዮጵያም እንድትገለገልበት መሠረት ይጥላል፡፡

## *6. <u>የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ አሠራር ባህርይ እና ተጓዳኝ ችግሮች</u>*

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሥርአት /TIN-System// አለም አቀፋዊ ባህርይ ያለው አሠራር ሲሆን፤ ያደጉም ሆነ በማደግ ላይ ያሉ ሃገራት ተግባራዊ በማድረግ ላየ ይገኛሉ፡፡ በማደግ ላይ ካሉ ሃገራት ጐረቤቶቻችን ኬንያ፣ ኡጋንዳ፣ ታንዛኒያ የመለያ ቁጥር /TIN/ አሠራራቸውን በዘመናዊ የኮምፒዩተር ቴክኖሎጂ በመታገዝ ግብር ከፋዮቻቸው በግብር ከፋይነት የሚለዩበት ልዩ መለያ ቁጥር እንዲኖራቸው በማድረግ የግብር አስተዳደራቸውን ቀላል ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን አስችሏቸዋል፡፡

በሃገራችንም ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 286/94 በሕግ የተደነገገ የግብር ከፋዩ መለያ ቁጥር /TIN/ አሠራርን ተግባራዊ በማድረግ እስከ አሁን ከ433000 /ከአራት መቶ ሰላሳ ሦስት ሺህ/ በላይ ግብር ከፋዮች የመለያ ቁጥር ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ለመስጠት ተችሏል፡፡

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ይዘት ተከታታይነት ያለው ባለ አሥር አሀዝ ቁጥር ሆኖ ባልተደጋገመ መልኩ ለእያንዳንዱ ግብር ከፋይ በኮምፒዩተር የመረጃ ሥርአት የሚሰጥ ቁጥር ነው፡፡ አንድ ግብር ከፋይ በኢትዮጵያ ውስጥ የትም ይኑር የት ብዙ የንግድ ድርጅቶች ቢኖረውም ባይኖረውም አንድ መለያ ቁጥር ብቻ ይሰጠዋል፡፡ ግብር ከፋዩ በዚህ መለያ ቁጥር በየትኛውም ቦታ /የሃገር ክልል/ የንግድ ሥራውን ሲያካሄድ በተሰጠው ቁጥር ማንነቱ ይለያል፡፡ መለያ ቁጥር የማይደጋገም /unique/ በመሆኑ ይህ ልዩ ቁጥር በንግድ ፈቃድ ላይ በፈቃድ ሰጪ መ/ቤቶች እንዲመዘገብ ይደረጋል፡፡

ይሁን እንጂ ባለፉት አምስት አመታት በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ አሠራርና አጠቃቀም ረገድ ችግሮች መከሰታቸው አልቀረም፡፡ ከችግሮቹ ዋነኛው የግብር ከፋይ ማንነት በመመዝገብ ቁጥር የሚሰጠው የኮምፒውተር ሥርአት ግብር ከፋዩን የሚለየው በስሙ በመሆኑና ወደፊት ሁሉም ክልሎች በየራሳቸው የስራ ቋንቋ መገልገል እስኪጀምሩ ድረስ ባሁኑ ወቅት የኮምፒውተር ሥርአቱ የሚጠቀምበት ቋንቋ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስለሆነ የአንድ ፊደል ለውጥ ወይም ግድፈት እንኳ ቢያጋጥም ፡-

ለምሳሌ፡- አቶ ዘርኡ ለማለት Ato Zeru ወይም Ato Zerue ወይም Ato Zeroo ተብሎ ከተጻፈ /ሁሉም ያስኬዳሉ/ አንዱን ሰው እንደ ሶስት ተመዝጋቢ አድርጎ በመውሰድ የተለያዩ ሶስት መለያ ቁጥር የመስጠት ችግር አጋጥሟል፡፡

ይህን ክፍተት በመጠቀም አንዳንድ ግብር ከፋዮች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ወደገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት በሚመጡባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ፎርም በመሙላት ፡-

- የራሳቸውን ስም፣ያባት ስም፣ የአያት ስም፡ የአያት ወይም የእናት ስም ፊደል በመቀየር፣
- የተለያዩ ድርጅቶች ባለቤት በመሆን ለእያንዳንዱ ድርጅት አንዳንድ መለያ በመውሰድ፣
- በአንድ ቤት ቁጥር የተለያየ ንግድ ፈቃድ በማውጣትና ለእያንዳንዱ ንግድ ፈቃድ አንድ አንድ መለያ ቁጥር በመያዝ

* ለተለያዩ ቅርንጫፎቻቸው የተለያየ መለያ ቁጥር በመውሰድ በህግ ከተደነገገው በተቃራኒ የተለያዩ ተደጋጋሚ ከአንድ በላይ መለያ ቁጥሮችን /Tin duplicate/ መያዝ መቻላቸው ታውቋል፡፡

ይህም የግብር ከፋይ  የመለያ ቁጥር የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን በአግባቡ በመጠቀም የግብር አስተዳደርን ቀልጣፋ ለማድረግና ታክስን ፍትሀዊ በሆነ መንገድ በአግባቡ በመሰብሰብ የተቀመጠውን ዓላማና ግብ ውጤታማ ለማድረግ አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ ስለዚህ ይህንና መሰል ችግሮችን ለመቅረፍ ለግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ከመስጠት ጐን ለጐን የአካላዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን /Biometric System/ ማለትም በጣት አሻራ /finger print/ የግብር ከፋይን ማንነት በማያወላዳ ሁኔታ የሚለይበት ሁኔታ ማካተት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 7. *የግብር ከፋይ መለያ አካላዊ የጣት አሻራ / Biometric finger print System/ መረጃ አያያዝ ሥርዓት*

የጣት አሻራ / finger print/ ማለት የጣት ውስጣዊ ፈለግ ወይም ጭረት ማለት ሲሆን ይህ አሻራ የአንድ ግለሰብ የግሉ የሆነና ከማንም ጋር /መንታ እንኳ ቢሆን/ የማይጋራው ልዩ የሥነ ተፈጥሮ መለያው ነው፡፡ ይህ አካላዊ የጣት አሻራን መረጃ አጠቃቀም ዘዴ ከጥንት ጀምሮ ምናልባትም ከክርስቶስ ልደት በፊት 6000 ዓመት ዓለም ጀምሮ በአሶሪያውያን፣ በባቢሎናውያን፣ በቻይናውያንና በጃፓናውያን የተለመደ አሰራር ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት በሌላው ዓለም አሻራን ለፓስፖርትና ቪዛ፣ለወንጀል ክትትል፣ ለማህበራዊ ደህንነት፣ለሰራተኛ ቅጥር፣ ለክሬዲት ካርድ፣ ለጡረታ እና ለግብር ከፋይ መለያነት ይገለገሉበታል፡፡

የሌሎች ሃገሮች ተሞክሮ እንደሚያሳየው ግብር ከፋይን በመለየት ረገድ አሁን ኢትዮጵን የገጠማት ችግር ገጥሟቸው እንደነበርና፣ ከችግሩ የተላቀቁት ከነባሩ አሰራር በተጨማሪ የጣት አሻራ የአሰራር ሥርዓት ዘርግተው ስራ ላይ በማዋላቸው  የግብርና ታክስ አስተዳደራቸው ውጤታማ እንዲሆን አስችሏቸዋል፡፡

በሃገራችን የጣት አሻራ አጠቃም ከጥንት ጊዜ ጀምሮ የቆየ ነባር ባህላዊ አሰራር ነው፡፡ማንኛውም የውል ሰነድ/ የብድር፣ የውርስ፣የግዢና ሽያጭ ውሎች፣ የሰላምታ ደብዳቤ/ እንዲሁም ለመንግሥት የሚቀርብ ማመልከቻ ሳይቀር በጣት አሻራ ተፈርሞ በቀረበ ቁጥር ተቀባይነቱና ተአማኒነቱ በህዝብ ዘንድም ይሁን በህግ ፊት ዋጋ ያለው ሆኖ እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ ሲሰራበት መቆየቱ በህይወት ያሉ አበው

ያረጋግጣሉ። በዚህ መልኩ ቻይናውያን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ3ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ይጠቀሙ እንደነበር የዘርፉ ሰነዶች ያመለክታሉ። ይሁን አንጂ የጣት አሻራ ፊለግን በመጠቅም ማንነትን በቀላሉ መለየት የመቻሉን ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ተገንዝበው ስለመጠቀማቸው የተለያዩ ሳይንቲስቶች የተለያየ አስተያየት አላቸው።

በዚህ መልኩ በተለይም ከ1684 ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከፍተኛ መሻሻል እየተደረገበት መጥቶ በአሁኑ ወቅትም በጣም ዳብሮና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እየተጋዘ በሁሉም መስክ ተፈላጊነቱ እየጎላ መጥቷል። አሁን አለም በደረሰበት ከፍተኛ የስልጣኔ ደረጃም የጣት አሻራ በዕለት ተዕለት ኑሮአችንና በኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ውስጥ ያለው ድርሻ የላቀ ነው። ያለንበት የኮምፒውተር ዘመን በኮምፒውተር እገዛ ግዢ የሚፈጸምበት፣ገንዘብ የሚንቀሳቀስበት፣ ውል መዋዋል፣ብድር መበደር፣መረጃ መስጠትና መቀበልን የመሳሰሉት ተግባራት የሚከናወኑበት ወቅት በመሆኑ ከዚህ ጋር የተአማኒነትና የሚስጢራዊነት ጉዳዮች አብሮ ይነሳሉ። በመሆኑም በጣት አሻራ የተደገፈን ዘመናዊዉን አሰራር አታሎ ወይም መረጃን ቀይሮ ለማጭበርበር የማይቻል ነገር ሆኗል።ስለሆነም ይህ አካሄድ በሀገራችን ተግባራዊ እንዲሆን ከወዲሁ የቅድመ ዝግጅት ሥራ መስራት የጠበቅብናል።

## 8. <u>በሃገራችን የጣት አሻራ መለያ ቁጥር አጠቃቀም ሁኔታ</u>

የሃገራችን የሚታየው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የድግግሞሽ /TIN Duplicate/ ችግር አለም አቀፋዊ ችግር ነበር። ሌሎች ሃገሮች ይህን ችግር የፈቱት በጣት አሻራ ላይ የተመሠረተ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አሠጣጥ ሥርዓትን ተግባራዊ በማድረግ በመሆኑ በእኛም ሃገር ይኸንን ተግባራዊ ማድረግ ግድ ይላል። በመሆኑም በ2001 ዓ.ም. በሃገራችንም ማንኛውም ግብር ከፋይ በጣት አሻራ ላይ የተመሠረተ የመለያ ቁጥር እንዲኖረው ይደረጋል

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 43፣44፣45፣52፣53፣ እና 91 የተደነገጉትን የግብር ከፋይ መለያ የመያዝ አስፈላጊነት እና እያንዳንዱ ግብር ከፋይ አንድ መለያ ቁጥር ብቻ እንዲይዝ ህግ ግዴታ የጣለበት በመሆኑ ከድግግሞሽ የጸዳ የግብር ከፋይ

መለያ ቁጥር ሥርአት እንዲዘረጋ እያንዳንዱ ተመዝጋቢ የጣት አሻራ በመስጠት ህጋዊ ግዴታውን እንደሚወጣ ይጠበቃል፡፡

## 9. የጣት አሻራ መለያ ቁጥር ዓላማ

* የማንኛውንም ግብር ከፋይ የጣት አሻራ /የግራና ቀኝ አመልካች ጣት አሻራ በኤሌክትሮኒክስ መስሪያ/ መዝግቦ ለመያዝ፣
* የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርን በጣት አሻራ መለያ በበለጠ ዘመናዊና አስተማማኝ ለማድረግ፣
* የግብር ከፋዩን ማንነት በርግጠኝነት መለየት እንዲቻል በጣት አሻራ የተደገፈ አስተማማኝ የግብር መረጃ እንዲኖር ለማድረግ፣
* ቀደም ሲል ያጋጥሙ የተመሳሳይ ስም ችግሮችን በጣት አሻራ አመዘጋገብ ዘዴ ለማስወገድ፣
* እንደ አስፈላጊነቱ መንግሥት ወደፊት ለሚጠቀምባቸው ሌሎች ሥራዎች በሀገር ደረጃ የተዘጋጀ የመረጃ መሠረት ለመጣል፤

## 10. የጣት አሻራ መለያ ቁጥር አስፈጊነትና ፋይዳ

አካላዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት /Biometric system/

* ስም በመቀያየር /የኮምፒዩተር ሥርዓቱ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ስለሚሠራ/ የስም ለውጥ በማድረግ የሚከሰቱ ችግሮች ማስወገድ፣
* የተለያዩ ድርጅቶች ባለቤት በመሆን ለእያንዳንዱ አንዳንድ መለያ መውሰድን ለማስቀረት፣
* በአንድ የቤት ቁጥር የተለያዩ የንግድ ፈቃድ በማውጣት በእያንዳንዱ የንግድ ፈቃድ የተለያየ መለያ ቁጥር መያዝን ማስቀረት፣
* በተለያዩ ምክንያቶች ማለትም ገቢ ለማሳወቅ ለመክፈል ፣ ክሊራንስ ለማውጣት ወደ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በሚመጡበት ጊዜ ፎርም በመሙላት ተጨማሪ መለያ ቁጥር መውሰድን ለማስቀረት
* በፌዴራልና በክልሎች ቅርንጫፍ ድርጅቶች ያሏቸው ግብር ከፋዮች ለእያንዳንዱ ቅርንጫፍ የተለያየ መለያ ቁጥር መያዝን ለማስቀረት፤ እንዲሁም በግብር ከፋዮች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ሲፈጠሩ የነበሩ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል ብቸኛ ዘመናዊ ዘዴ በመሆኑ አስፈላጊ ነው፡፡

## *11. በጣት አሻራ መለያ አሰጣጥ ሂደት ዋና ዋና ተግባሮች*

### *ሀ/ መረጃ አወሳሰድና አመዘጋገብ*

* አዲስ ግብር ከፋዮች የግብር ከፋይ መለያ ቁር ፎርም መሙላት
* ነባር የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ያላቸው ስምና ቁጥራቸውን ብቻ በተዘጋጀው ፎርም መሙላት፤
* ተማሪዎች ለነሱ የተዘጋጀ አጭር ፎርም መሙላት
* የግብር ከፋዩን ምስል /ፎቶ/ እና የግራ ቀኝ አመልካች ጣቶችን አሻራ በዘመናዊ ዘዴ /electronically/ መውሰድ
* በተለያየ ምክንያት የጣት አሻራ የተጐዳ ወይም የተሳሳተ ሊሆን ስለሚችል የአሻራውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ
* የተወሰደውን የጣት አሻራና የፎቶግራፍ ምስል ከሌሎች የግብር ከፋዮች ዝርዝር መረጃዎች ጋር ማጣመር
* ከየትኛውም የግብር መሰብሰቢያ ቦታ የተላከውን /የተገኘውን የግብር ከፋዩን ሙሉ መረጃ በማዕከላዊ ዋና መረጃ ማከማቻ/ቋት እንዲቀመጥ ማድረግ
* መረጃው በግብር ሰብሳቢው በለሥልጣን ደረጃውን በጠበቀ የፋይል አያያዝ እንዲጠበቅ ማድረግ
* በብዙኃን መገናኛ ወደፊት በሚገለፅ በአንድ በተወሰነ ቦታ ቀርቦ የጣት አሻራ መስጠት

### *ለ/ መረጃዎችን ማረጋገጥ*

ቀደም ሲል የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ተሰጥቷቸው በተለያዩ ምክንያት /ቢጠፋባቸው ወይም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ድጋሚ ለመውሰድ/ እንደገና ለሚጠይቁ

* የጠያቂውን ማመልከቻ ተቀብሎ የጣት አሻራና ፎቶ ሙውሰድ
* የተወሰደውን አሻራና ምስል ወደዋናው ማዕከላዊ የመረጃ ማዕከል በመላክ ተመሳሳይ መረጃ መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ
* ከዋናው ማዕከላዊ የመረጃ ማዕከል በተገኘው ምላሽ መሠረት ከየትኛውም የግብር መሰብሰቢያ ማዕከል በመሆን ተገቢውን አገልግሎት መስጠት ይቻላል፡፡

## 12. ማጠቃለያ

የግብር ከፋይ መለያ አሰጣጥን በቁጥር እና በጣት አሻራ አቀናጅቶ መጠቀም የተጀመረውን ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር በማጠናከር ውጤታማ ለማድረግ ከማስቻሉም በላይ ግብር ከፋዩን ለይቶ በማወቅ ስለግብር ከፋዩ የሥራ እንቅስቃሴ የሚያስረዱ መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችልና በዚሁ ላይ ተመስርቶም የግብር አወሳሰንና አሰባሰብ አፈፃፀም እንዲሁም አጠቃላይ የአገልግሎት አሰጣጡን በዘመናዊ አሠራር በማገዝ ቀልጣፋ አስተማማኝ ያደርገዋል፡፡ በዚህ መልክ የሚሰበሰብ መረጃ የበለፀጉ ሃገራት እንደሚያደርጉት ሁሉ መንግስት ለሚሰጠው ማህበራዊ ደህንነት ዋስትና መረጃ እንደመነሻ ሊጠቅም እንደሚችል በመገንዘብ ይህ ዘመናዊ የአሰራር ዘዴ /Biometric system/ በሃገራችን ተግባራዊ እንዲሆን ሁሉም የድርሻውን በማበርከት ውጤታማ እንዲሆን የበኩሉን ጥረት ሊያደርግ ይገባል ፡፡

ይህንን ዘዴ /Biometric Tax payer identification system/ ተግባራዊ ለማድረግ በአዲስ አበባ የሚገኘው የኢትዮጵያ ገቢዎችን ጉምሩክ ባሥልጣን ዋና ማዕከሉ ሆኖ በመጀመሪያ ዙር በአዲስ አበባ መስተዳድር ሥር ባሉት አሥር ክ/ከተሞችና ቀበሌዎች፣ በሁሉም የክልል ማዕከላት /የድሬደዋን ከተማ መስተዳድር ጨምሮ/፣ እና በተለያዩ የሃገሪቱ ክልሎች በሚገኙ በተመረጡ 500 ወረዳች በአንድ ነጥብ ስድስት /1.6/ ሚሊዮን ግብር ከፋዮች ላይ የሚተገበር ሲሆን፤ ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀ በኂላም ለአዲስ ተመዝጋቢዎች በተከታታይነት የሚቀጥል አሰራር ነው፡፡